ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር
የባለአክሲዮኖች 7ኛ ድንገተኛ ጉባኤ
ቃለ ጉባኤ ቁጥር 7

ድንገተኛ

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ:- አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ አዳራሽ (አዲስ አበባ)
ቀን:- ህዳር 30, 2011 ዓ.ም.
ሠዓት:- ከጠዋቱ 3:00 - 6:30

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 7ኛድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ህግ አንቀጽ 392 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 15 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE 467/18 በOCTOBER 29/2018 በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ በተጨማሪም በስልክ ተጠርተዋል፡፡

3. የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት እና በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች

3.1 የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት፣

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | ወ/ሮ ጽጌ ኃይሌ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 3 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የጉባኤው ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት | የአስተዳዳሪው ወይም የተወካይ አስተዳዳሪ ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | ወ/ሮ ጸሐይ ፀጋዬ ማተ | የቦርድ አባል | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ አክሊሉ ታደሠ | የቦርድ አባል | |

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa Branch Office

National Bank of Ethiopia

### 3.3 በጉባኤው ያልተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | የቦርድ አባል |
| 2 | አቶ መስፍን ተፈራ | የቦርድ አባል |
| 3 | አቶ ኤፍሬም አላምረው | የቦርድ አባል |

### 3.4 በጉባኤው የተገኙ ታዛቢዎች

| ተ/ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ይትባረክ መዘምር | ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማይክሮ ፋይናንስ ሱፐርቪዥን ዳሬክቶሬት |

4. ምልዓተ ጉባኤ፣
   - 4.1. ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 16
   - 4.2. ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 25,000
   - 4.3. በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት11 የያዙት አክሲዮን ብዛት22176 ( 88.704%)
   - 4.4. በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 5 የያዙት አክስዮን ብዛት 2824 (11.296 %)
   - 4.5. ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 12,500 (50 %)

በዚሁ መሰረት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 6 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 425 መሠረት ከማኅበሩ ባለአክስዮኖች 88.704% አባላት የተገኙ ስለሆነ በጉባዔው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሣኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡

በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር እና የያዙትን የአክስዮን መጠን የሚገልጽ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet 1) (ሠንጠረዥ-1) ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

በንግድ ህግ አንቀጽ 405 መሠረት በጉባኤው ላይ ለድምጽ ቆጣሪነት ከባላአክሲዮኖች ውስጥ ብልጫ አክሲዮን ያላቸው ሁለት አባላት ድምጽ ቆጣሪ ሆነው እንዲመረጡ ተጠይቆ፣ የአክሲዮን ብልጫ ያላቸው ከማህበሩ አባላት ውስጥ ሁለት አባላት ብቻ ሲሆኑ እነዚህ አባላት የቦርድ ሰብሳቢ እና የቦርድ አባል በመሆናቸው ጠቅላላ ጉባኤው ለድምጽ ቆጣሪ እንዲመርጥ ሲሉ አባላት ሀሳብ በመስጠታቸው ሁለት ድምጽ ቆጣሪ በምርጫ ተመርጠዋል፡፡

5.የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. የጉባኤውንአጀንዳማጽደቅ፤
5.2. የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ መወሰን
5.3. የኩባንያውን መጠሪያ ስም ስለመቀየር
5.4. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

6.1. አጀንዳ 5.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ

6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው በድንገተኛ ጉባኤው ላይ ሊነጋገርባቸው ይገባል በማለት የቀረቡትን አጀንዳዎች በዝርዝር በማስረዳት በጉባኤው ሊጨመር ወይም ከቀረቡት አጀንዳዎች ውስጥ ሊወጣ የሚገባ ካለ በመጠየቅ ለውሳኔ አቅርበዋል፡፡

6.1.2 ውሣኔ፣

የቀረቡት አጀንዳዎች የድንገተኛ ጉባኤ አጀንዳዎች በመሆናቸው እንዲሁም ከአጀንዳዎቹ ላይ ሊጨመር ወይም ሊወጣ የሚገባ አለመኖሩ ተረጋግጦ አጀንዳዎቹን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

7. አጀንዳ 5.2. የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ መወሰን

7.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ የማህበሩ ካፒታል ማደግ ያስፈለገበትን ዋና ዋና ምክንያቶች ለጉባኤው አባላት አቅርበዋል፡፡ እነዚህም የማህበሩ ካፒታል ማደግ የማህበሩን ገጽታ ይገነባዋል፤ ለበድር ፈንድ የሚሆን የባንክ ብድር ለማግኘት ያግዛል| የተቋሙን ዉጤታማነት ይጨምራል በሚሉ ሃሳቦች ዙሪያ አጀንዳዉ ላይ ዉይይት ተደርጓል፡፡

የካፒታል ጭማሪ የሚደረገው ተቋሙ መመሥረቻ አንቀጽ 7(መ) መሠረት ከተጠራቀመው አመታዊ የተቋሙ ትርፍ ላይ በመሆኑ የተቋሙ ካፒታል በዚያው መጠን እንዲያድግ ሃሳብ ለጉባኤው ቀርቧል፡፡

ጉባኤው የየጉባኤው ጽ/ቤት ያቀረበውን ከዚህ በላይ ያለ ሃሳብ ተቀብለው በእለቱ በጉባኤው ላይ ያልተገኙ ባለአክሲዮኖች አክሲዮናቸው በሌሉበት የማያድግላቸው መሆኑንና በሚፈልጉበት ጊዜ ማሳደግ እንደሚችሉ የባለአክሲዮንነት መብታቸዉ የተጠበቀ መሆኑን ጠቅሰው በቀባለው መሠረት የተቋሙ ካፒታል ቀድሞ ከነበረበት 25000.000 ወደ 30324.00 እንዲሆን ለጉባኤው ሃሳብ ቀርቦ በጉባኤዉ ላይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች በድምጽ ዉሳኔ ሰጥተዉ እንድያጸድቁ የጉባኤዉ ጽ/ቤት ሊቀመንበር ለዉሳኔ አቅርበዋል፡፡

7.2. ውሣኔ

ከዚህ በላይ በውይይቱ አጭር ቃል ላይ በቀረበው መሠረት ሆኖ የማህበሩ ካፒታሉ ከ25ሚሊዮን ወደ ሰላሳ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ አራት ሺህ እንድያድግ ጉባኤዉ በሙሉ

ሳይቀየር ፖቨርቲ ኢራዲኬሽን ኤንድ ኮሙኒቲ ኢፓወርንመንት የሚለዉ የምጻረ ቃል ፍቺው ቀርቶ በአማርኛው ፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር እንዲሆን በእንግሊዝኛው ደግሞ PEACE MICROFINANCE SHARE COMPANY ተብሎ እንዲጠራ በሚል ለጉባኤው ሃሳብ የቀረበ ሲሆን ጉባኤውም ስም ለገበያ ዋና አስፈላጊ ከሆኑት አንዱ በመሆኑ አጠር ያለና ኩባንያዉ ፍቃድ ያገኘበትን የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ የተቋቋመበትን አላማ የሚገልጽ መሆኑ ጥሩ ነዉ በማለት በሙሉ ድምጽ ተስማምተዉ የጉባኤዉ ጽ/ቤት ለውሳኔ እንዲያሳልፈው ጠይቀዋል፡፡

7.3.2 ውሣኔ

አክሲዮን ማህበሩ ቀድሞ ይጠራበት የነበረው ፖቨርቲ ኢራዲኬሽን ኤንድ ኮሚኒቲ ኢምፓወርመንት/ Poverty Eradication and Community Empowerment/ የሚለው የምጻረ ቃሉ ፍቺ ቀርቶ በአማርኛው ፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ብቻ እንዲሆን በእንግሊዝኛው ደግሞ PEACE MICROFINANCE SHARE COMPANY ብቻ ተብሎ እንዲጠራ በሙሉ ድምጽ ተወስኗል፡፡

8. አጀንዳ 5.4 የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ

8.1 የውይይቱ አጭር ቃል

ህዳር 22 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገው የፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አ.ማ ድንገተኛ ጉባኤ፣ ጉባኤው የተነጋገረበትን ቃለ ጉባኤ በዝርዝር ተመዝግቦ በእያንዳንዱ በጉባኤው በተገኘ አባል ተፈርሞ እንዲቀመጥ ወስኗል፡፡

8.2 ውሣኔ

ጠቅላላ ጉባኤው ቃለ ጉባኤው ከተነበበለት በኋላ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

9. ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች

9.1 የማህበሩ መመሥረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ

10. የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ማረጋገጫ

እኛ የፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣ የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በየስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በህዳር 22 ቀን 2011 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 7ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውንና በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔዎች ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን አረጋግጠናል፡፡

| ተ/ቁ | የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር እና የጉባኤው ሰብሳቢ | |
| 2 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃማርያም | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 3 | ወ/ሮ ጽጌ ኃይሌ | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የጉባኤ ጽ/ቤት ፀሐፊ | |

11. የአስተዳዳሪዎች ማረጋገጫ

እኛ የፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር አስተዳዳሪዎች ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣ የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በህዳር 22 ቀን 2011 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 7ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውንና ራሳቸዉ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔዎች ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን አረጋግጠናል፡፡ በሰነዶቹ ላይ ስለተገፁት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ዉሳኔዎች ትክክለኛነት ስማቸዉ በሰነዶቹ ላይ የተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸዉም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት | የአስተዳዳሪው ወይም የተወካይ አስተዳዳሪ ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | ወ/ሮ ጸሐይ ፀጋዬ ማተ | የቦርድ አባል | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ አክሊሉ ታደሠ | የቦርድ አባል | |

New

በፌ.ዴ.ሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ አዲስ አበባ የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Ten Office)

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)

ቁጥር ቅ10/283/ዓኢ/11

በፊቴ ቀርበው ፈርመዋል

አዲስ አበባ 11/11 ቀን 20 11 ዓ.ም

መኑር መሐመድ አህመድ
የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ
Menur Mohammed Ahmed
Branch Manager

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለበት ምክንያት ______

የገንዘብ ልክ ብር 162

ሳንቲም ______

ወይም ብር ______ የሆነ ቴምብር ተለጥፏል

የደረሰኝ ቁጥር 1146669

11/11 ቀን 20 11 ዓ.ም

የቴምብር ቀረጥ መብት አስከባሪ

ስም ______

ፊርማ ______